ስረጭት 1.1

አባሪ: ለኖርዌጂያን ቋንቋ ስልጠና መመሪያ

# የኖርዊጂያን ቋንቋንና የኖርዊጅያን ማሕበረሰብ ለማወቅ ብቃትን የሚሰጥን ስልጠና ተካፋዮች መግለጫ

## ስለ እርስዎ የኖርዊጅያን ቋንቋ ስልጣና ዕቅድ

- እርስዎ እና አውራጃው ወይም ኳሚውኑ በመተባበር የኖርዊጅያን ቋንቋ ስልጠና እቅድ ለእርስዎ የኖርዊጂያን ቋንቋ እና የኖርዊጅያን ማሕበርሰብ ስልጣና ላይ ተካፈይነት እቅድን ታወጣላችሁ። ስልጠናው ጥሩ የኖርጂያን ቋንቋ ክህሎቶችን እንዲያገኙ ፣ የኖርዌ ማሕበረሰብ ሕይወት በቂ ዕውቀት እንዲያገኙ እና ከሥራ ሕይወት ጋር ዘላቂ ግንኙነት እንዲያገኙ አስተዋጽኦ ያበረክታል ፡፡

## የኖርዌይ ቋንቋ ስልጠና የርሶ ግብ

- በኖርዊጂያ ቋንቋ ሥልጠና ተሳታፊዎች በኖርዊጅያን ቋንቋ ዝቅተኛ ደረጃውን ቢያንስ መድረስ አለባቸው ፡፡ ተሳታፊዎች የአውራጃው ገዢና እና አውራጃው ወይም ኳሚውኑ ይኽንን ዝቅተኛውን ደረጃ ተብሎ የታቀደውን የቋንቋ እውቀት ብቃት እንዲያገኝ አስፈላጊውን ያደርጋሉ ወይም ያቀርባሉ። ይኽ ዝቅተኛው ደረጃ የተሳታፊው የኖርዊጅያን የቋንቋ ግብ ነው።

## የሥልጠና ቀነ-ገደቧች እና የስልጠናው ወሰን ወይም መጠን

- በኖርዊጂያን የቋንቋ እና በኖርዊጅያን ማሕበረሰብ ትምህርቶች ሥልጠና የመሳተፍ መብትና ግዴታ የሚሰጥ የመኖሪያ ፈቃድ ያላቸው ሰዎች ተሳታፊነታቸው በኖርዊጂያን ቋንቋ ቢያንስ የመጨረሻ ዝቅተኛው ደረጃው እስኪደረስ ነው። ይኽም ማለትም የተሳታፊው የኖርዊጂያን ቋንቋ ግብ እስኪ ደርስ ድረስ ይካፈላል ማለት ነው ፡፡ ሆኖም ግን ሥልጠናው የተፈቀደ የፈቃድ ወቅቶችንም ጨምሮ ከሦስት ዓመት በላይ ሊቆይ አይችልም ፡፡

- አንድ ተካፋይ ቀደም ብሎ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ወይም ከዛም በላይ የሆነ የትምሕርት ደረጃ ያለው ተሳታፊ በፈቃድ የተወሰደን የእረፍት ገዜንም ጨመሮ ከ18 ወር በላይ በስለጠናው ላይ የመካፈል መብትም ሆነ ግዴታ የለውም ፡፡

- በኖርዊጂያን ቋንቋ እና በማሕበረሰብ ትምህርት ሥልጠና የመሳተፍ ግዴታ ያለባቸው ተሳታፊዎች ተሳታፊው በኖርዊጅያን ቋንቋ ዝቅተኛ ደረጃውን (የተካፋዩን የኖርዊጂያን ቋንቋ ግብ) እስኪደረስ ድረስ ወይም የኖርዊጂያን ቋንቋ ሥልጠናው 300 ሰዓታት እስኪያጠናቅቅ ድረስ የሥልጠና ግዴታው አለበት፡፡

- የኖርዊጂያን የማሕአበረሰብ ጥናት ሥልጠና ተሳታፊው በሚረዳው ቋንቋ መሰጠት አለበት ፡፡ መብቱ እና ግዴታው ተወስኖ ከጸናበት ቀን አንስት ሥልጠናው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ አለበት ፡፡ ይኽ ግን የአውራጃው ግዢው ለማህበራዊ ትምህርት ሥልጠና በሚሰጥበት ጊዜ ስራ ላይ አይውልም ፡፡

## ከተካፋይነት መቅረት እና ከተካፋይነት ፈቃድ

ከኖርዊጂያን ቋንቋ እና የኖርዊጂያን ማሕበረሰብ ትምህርቶች ስልጠናው ከተካፋይነት ለመቅረት ፈቃድ ለማግኘት ለአውራጃው ወይም ለኳሚውኑ ማመልከት ይቻላል ፡፡ (የተለዩ ድንጋጌዎች በሕግና በደንቦች እንዚሕ የተቀመጡ ናቸው ፡፡ ) imdi.no የተባለውን ድሕረ ገጽ ይመልከቱ ፡፡

## ስለ ስልጠናው መቆረጥ

- አውራጃው በግለሰባዊ ሁኔታ ተጨባጭነት ያለው በቂ ምክንያት ያለው ከሆነ ስልጠናውን ለጊዜው ወይም በቋሚነት ተሳታፊው እንዳይሳተፍ ሊያግድ ይችላል ፡፡ ሥልጠናውን ለማቆም በቂ ምክንያት ሊሆኑ ከሚችሏቸው ሁኔታዎች መካከል ሰፋ/ ብዛት ያለው ከተካፋይነት መቅረትን ፣ የተሣታፊው ጸባይና ድርጊት የራሱ የተሳታፊውን ሆነ የሌሎችን ተሳታፊዎች ሥልጠናው ፍጻሜ የመድረስን እድልን የየሚያሰናክል ከሆነ ወይም ተካፋዩ የከባድ ወይም የረጅም ጊዜ ሕመም ተጠቂ በሚሆንበት ጊዜዎች እንደሚሳሌ ሊወሰዱ ይችላሉ ፡፡

*ፈተናዎች*

- ለኖርዊጂያን ቋንቋ  እና በማሕበረሰብ ትምህርቶች ሥልጠና የመሳተፍ መብትና ግዴታ የሚሰጡ የመኖሪያ ፈቃድ ያላቸው ተሳታፊዎች ለኖርዊጂያን ቋንቋ  እና በማሕበረሰብ ትምህርቶች ሥልጠና የመጨረሻ ፈተናዎችን የመውሰድ ግዴታ አለባቸው ፡፡

- ግዴታው ፈተናውን ከመወሰድ ነፃ ለሆኑ ተሳታፊዎችን አይመለከትም ፡፡ ተሳታፊዎች ማመልከቻ ከአቀረቡ በሁላ ፈተና(ዎችን) ከመውሰዳቸው ግዴታ ነፃ ሊወስጡ ይችላሉ ። አውራጃው በሕግና በደንቡ ውስጥ ባሉት ሕጎች መሠረት ማመልከቻዎችን አይቶ ይወስናል ፡፡

- በማሕበረሰብ ትምህርቶች ሥልጠና የመጨረሻ ፈተና መብትና ግዴታ ተወስኖ ከጸናበት ቀን  በኋላ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ አለበት ፡፡ (የአውራጃው ገዠ በማሕበረሰብ ትምህርቶች ሥልጠና  በሚሰጥበት ጊዜ ይህ ተግባራዊ አይሆንም) ፡፡

- አውራጃው የኖርዊጂያን ቋንቋ እና የማሕበረሰብ ትምህርቶች ሥልጠና  የመጨረሻ ፈተና የመውሰድ ግዴታ ያለባቸውን ተገቢውን ፈተና ለመወሰድ እንዲችሉ አስፈላጊውን ያቀርባል ወይም ያዘጋጃል።

## በኖርዊጂያን የቋንቋ ስልጠና ላይ ቅሬታን ወይም አቤቱታን ማቅረብን ይፈልጋሉ ወይ?

- ስለ የኖርዊጂያን የቋንቋ ስልጣና እቅድ ስለስልጠናውም ሆነ ስል ይዘት አቤቱታ ወይም ቅሬታ ከአልዎት ማቅረብ ይችላሉ ፡፡

*አቤቱታ ወይም ቅሬታ የሚያቀርቡ ከሆነ*

- ስለ የኖርዊጂያን የቋንቋ ስልጣና እቅድ ይዘት ውሳኔው ከደረስዎ በሁላ በሶስት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ቅሬታዎን ወይም አቤቱታዋን ያቅርቡ።
- የኖርዊጂያን የቋንቋ ስልጣና እቅድ ውሳኔ ለወሰደው ለሰጠው የአወራጃው ለሚገኘው የመንግስት አካል ቅሬታውን ያቅርቡ ።
- ቅሪታዋ ምን ላይ እንደሆነ በግልጽ ይግለጡ
- ቅሬታውን ከማስገባትዎ በፊት መፈረም አለብዎት

ጠበቃም ከአሎት እርስዎን ወክሎ ቅሬታ ማቅረብ ይችላል ፡፡ አንድ ሰው እንደ ተወካይዎ ሆኖ ለእርስዎ አቤቱታ እንዲጽፍሎት ለዚያ ግለሰብ በጽሑፍ ተወካይ ለመሆኑ ፈቃድ መስጠት አለብዎት ፡፡ይኽ የውክልና ስልጣን ላይ ውክልና የተሰጠው ግለሰብ እርስዎን ወክሎ ምን ምን ማድረግ እንደሚችል መግለጽ አለበት ፡፡ ጠበቃ ካለዎት የውክልና ስልጣን አያስፈልግም።

## ስለ የኖርዊጂያን የቋንቋ ስልጣና እቅድ  ተጨማሪ መረጃ ከየት ማግኘት ይችላሉ?

ስለ ውህደት እቅድ ተጨማሪ መረጃ ስለ ውህደት በወጣው ህግ ውስጥ ይገኛል ፡፡ ህጉ አብሮ ሆኖ ከወጣው የጹሁፍ ስርጭቶች ጋር በ www.imdi.no እና በኖርዌ በብቃት ድረ ገጽ ወይም (Kompetanse Norge nettsider) ያገኛሉ።

በስልጣናው ላይ መልካም ዕድል እንመኛለን!